ምክንያተ ፡ ጽሒፈቱ ፡ ለሐዋርያ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ረድኡ ።

እስመ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ኀደጎ ፡ ቀዳሚ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ በኤፌሶን ፡ አመ ፡ የሐውር ፡ መቄዶንያ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ጳጳሳተ ፡ ወቀሲሳነ ፡ ለለአህጉር ፡

ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በአቴና ፡ እንዘ ያጤይቅ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ግእዘ ፡ ጳጳሳት ፡ ወቀሲሳን ፡ ወዘከመ ፡ ይደልዎሙ ፡ ይሠየሙ ።

ለዕቤራትሂ ፡ ወለመበለታት ፡ አለበዎ ፡ ዘከመ ይደሉ ፡ ይንበራ ፡ ምስሌሁ ፡ እው ፡ ይትገኃሣ ።

ወዓዲ ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ ይኩኖሙ ፡ አርዓያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለመሃይምናን ፡ በቃሉ ፡ ወበምግባሩ ።

ወይርኃቅ ፡ እምኵሉ ፡ ፍትወተ ፡ ውርዘውት ወያግርር ፡ ርእሶ ፡ ለጽድቅ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ።

ወፈነወ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ፡ ረድኡ ።

ጳውሎስ ፡ ለደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ለጢሞቴዎስ መጀመሪያይቱን ፡ ክታብ ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት፤

ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ለያገሩ ፡ ጳጳሳትን ፡ ቀሳውስትን ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ በኤፌሶን ፡ ትቶት ፡ ሒዶ ፡ ነበርና ።

የጳጳሳት ፡ የቀሳውስት ፡ እንዋራቸው ፡ እንደምን ፡ እንደኾነ ፡ እንደምን ፡ ያሉት ፡ ሊሾሙ ፡ እንዲገባቸው ፡ ሲያስረዳ ፡ በአቴና ፡ ኹኖ ፡ ጻፈለት

ከባልቴቶች ፡ ሴቶችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሲኖሩ ወይም ፡ ሲለዩ ፡ የሚገባቸው ፡ እንዴት ፡ እንዴት ያሉት ፡ እንደኾኑ ፡ ሲያስገነዝብ ፡ ጻፈለት ።

ዳግመኛም ፡ በሥራው ፡ በአነጋገሩ ፡ ለምእመናን ፡ በጎ ፡ እብነት ፡ መልካም ፡ አርዓያ ፡ ይኾናቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ።

ጉልምስና ፡ ከሚያመጣው ፡ ፍትወት ፡ ኹሉ እንዲርቅ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ራሱን ፡ ለጽድቅ፣ እንዲያስገዛ ፡ አዝዞታል ።

ይህንም ፡ ክታብ ፡ በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ በቲቶ እጅ ፡ ላከለታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ጢሞቴዎስ ፣ የልስጥራን ፣ ሰው ፣ ነው ፣ አባቱ ፣ አረማዊ ፣ ነው ፣ እናቱ ፣ አይሁዳዊት ፣ ናት ፣ በጳውሎስ ፣ ስብከት ፣ አምናለች ፣ ወእሙሰ ፣ አይሁዳዊት ፣ ወአምነት ፣ እንዲል ። ግብ ፣ (ሐዋ ፣ ፲፮ ፣ ፩ ።)

በኋ ፣ ብላቴንነቱን ፣ አይቶ ፣ ሲሻው ፣ አይቶ ፣ ከፍጹምነት ፣ እንዲደርስ ፣ ፀውቶ ፣ ሊከተሉታል ፣ ሲያ ስከትለውም ፣ ግዝሮ ፣ አስከትሎታል ፣ ወገዘሮ ፣ ለጢሞቴዎስ ፣ በእንተ ፣ አይሁድ ፣ እለ ፣ ውስቴ ፣ ውእቱ ፣ ብሔር ፣ እንዲል ፣ (ግብ፣ ሐዋ፣ ፲፮ ፣ ፫ ።) ኋላም ፣ ከፍጹምነት ፣ እንደ ፣ ደረሰ ፣ ፀውቶ ፣ በኤፌሶን ፣ ኤጲስ ቆጶስነት ፣ ሹሞታል ። ኋላም ፣ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ያለውን ፣ ሹም ፣ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ያልውን ፣ አትሹም ፣ እያለ ፣ ሲያጸና ፣ ጽፎ ፣ ይሰድለታል ። እስተበቍዐከ፣ ቀዳሜ ፣ ዙሉ ፣ ትግበር ፣ ጸሎተ ፣ ወስእለ ፣ ወተጋንዮ፣ ወበእን ተዝ ፣ ጸልዩ ፣ ላዕለ ፣ ዙሉ ፣ ሰብእ ፣ ወላዕለ ፣ ዙሉ ፣ ነገሥት ፣ ወመኳንንት ፣ ይላል ። (ም ፣ ፪ ፣ ፩ ።)

ወከማሁ ፣ አንስትኒ ፣ ይትረሰያ ፣ ለጸሎት ፣ በፈሪሀ ፣ እግዚአብሔር ፣ ወበኃፍረት ፣ ወበልቡና፣ (ም ፣ ፪ ፣ ፱ ።) እሙን ፣ ነገር ፣ ዘይፈቅድ ፣ ይሠየም ፣ ጳጳስ ፣ ሠናየ ፣ ግብረ ፣ ፈተወ ፣ ይላል ። (ም ፫ ፣ ፩ ።ወዲያቆ ናትኒ ፣ ከማሁ ፣ ንጹሐን ፣ ወእስትርኩባን ፣ እለ ፣ (፩ ፣ ቃሎሙ ፣(ም ፫ ፣ ፱ ።)

እለ ፣ ሠናየ ፣ ይትለአኩ ፣ እንተ ፣ ቴዐቢ ፣ ሢመተ ፣ ይገብሩ ፣ ሎሙ ፣ (ም፣ ፫ ፣ ፲፫ ። ዑቅ፡ርእስከ፣ በእ ንተ ፣ አንብቦ ፣ ወዘልፈ ፣ ሀሉ ፣ ባቲ ፣ ይላል ፣ ሊቃናተ ፣ ኢታመንኖ ። ም ፣ ፭፣ ፩ ።)

አክብር ፣ ዕቤራተ ፣ በጽድቅ ፣ ይላል። (ም፣ ፭፣ ፫ ።)

ወለእመ ፣ ኀረይከ ፣ ዕቤረ ፣ ኀረይ ፣ እንተ ፣ ፷ ፣ ከረምታ ፣ ይላል ። (ም፣ ፭፣ ፱ ።)

እለ ፣ ሠናየ ፣ ተልእኩ ፣ ቀሲሳን ፣ ምክዕቢተ ፣ ክብር ፣ ይደልዎሙ ፣ ይላል ። (ም ፣ ፭ ፣ ፲፯ ።)

ላዕለ ፣ ልሒቅ ፣ ኢትስማዕ ፣ ውዴተ ። (ም ፣ ፭፣ ፲፱ ።)

ወኢታጽድቆ ፣ ለሰብእ ፣ ቅድመ ፣ ፍትሕ ። ወኢትሢም ፣ ፍጡነ ፣ ወኢመነኒ ። (ም ፣ ፭፣ ፳፩ ።)

ኢትስተይ ፣ ማየ ፣ ዕራቆ ፣ ኅዳጠ ፣ ወይነ ፣ ቶስሕ ፣ ይላል ፣(ም፣ ፭ ፣ ፳፣ ፫ ።)

ከዚያም ፣ ለአብዕልተ ፣ ዝንቱ ፣ ዓለም ፣ አዝዞሙ ፣ከመ ፣ ኢይትአበዩ ፣ ወኢይትአመንዎ ። ለብዕሎሙ ፣ ኃላፌ ፣ ይላል ፣ (ም ፮ ፣ ፲፯ ፣) የተጻፈበት ፣ አገር ፤ አቴና ፣ ክታብ ወሳጅ ፣ ቲቶ።

ምዕራፍ ፣ ፩ ።

ክፍል ፣ ፩ ።

፩ ፣ እምጳውሎስ ፣ ሐዋርያሁ ፣ ለኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ በትእዛዘ ፣ እግዚአብሔር ፣ መድኃኒነ ፣ ወኢየሱስ ፣ ክር ስቶስ ፣ ቀስፋነ ። (ቆላ ፣ ፩ ፣ ፳፯ ።)

በመድኃኒታችን ፣ በእግዚአብሔር ፣ አብ ፣ ባለኝታችን ፣ በየኢሱስ ፣ ክርስቶስም ፣ ትእዛዝ ፣ ጸንቼ ፣ ብገኝ ። አንድም ፣ (በትእዛዘ ፣ እግዚአብሔር ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ መድኃኒነ ፣ ወተስፋነ) ፣ መድኃኒታችን ፣ አለኝታችን ፣ በሚኾን ፣ በእግዚአብሔር ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ትእዛዝ ፣ ጸንቼ ፣ ብገኝ ፣ ስውን ፣ አጸና ዘንድ ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ከሾመኝ ፣ ከኔ ፣ ከጳውሎስ ፣ የተላከች ፣ ክታብ ።

፪ ፣ ለጢሞቴዎስ ፣ ወልድየ ፣ ዘአፈቅር ፣ በሃይማኖት ። (ቲቶ ፣ ፩ ፣ ፬) ።

በሃይማኖት ፣ ጸንቶ ፣ ምግባር ፣ ሲሠራ ፣ ባገኘው ፣ ለምወደው ፣ ለልጁ ፣ ለጢሞቴዎስ ፣ ትድረስ ። ብዙ ፣ ሲወልዱ ፣ ሞያውን ፣ ምግባሩን ፣ አይቶ ፣ አንዱን ፣ ይወዱ ፣ እንዲሉ ።

ሰላም ፣ ለከ ። ቸር ፣ አለሀን ።

ወሣህል ። ይቅርታ ፣ ይደረግልሀ ።

ወጸጋሁ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ እቡነ ፣ ወእግዚእነ ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ።

የእግዚአብሔር ፣ አብ ፣ የጌታችን ፣ የኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ጸጋው ፣ ይደርብህ ፣ ይደረግልህ ።

፫ ፣ እስመ ፣ እስተብቋዕኩከ ፣ ትንበር ፣ ኤፌሶን ፣ እመ ፣ አሐውር ፣ መቄዶንያ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፣ ፳ ፣ ፩ ።)

ወደመቄዶንያ ፣ በሔድሁ ፣ ጊዜ ፣ በኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፣ ሹሜሃለሁ ፣ እኮ ።

ከመ ፣ ትገሥጾሙ ።

ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ በኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፣ ቆጶስነት ፣ ሹሜሃለሁና ፣ እን ዲህ ፣ የሾምሁህ ፣ ትመክራቸው ፡ ታስተምራቸው ፣ ዘንድ ፣ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ኢያምጽኡ ፡ ካልአ ፡ ትምህርተ ።
እኛ ፡ ካስተማርነው ፡ ትምህርት ፡ ሌላ ፡ እንዳያመጡ ፡ (አለ ፡) ኦሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ።

፩ ፡ ወኢያምጽኡ ፡ መኃድምተ ። (ም ፡ ፬ ፡ ፯ ።)
ተረት ፡ ኦሪትን ፡ እንዳያስተምሩ ። ተረት ፡ ለራት ፡ መቆያ ፡ እንደኾነ ፡ ኦሪትም ፡ ለወንጌል ፡ መቆያ ፡ ናትና ።
ወዛውዐ ፡ ነገር ፡ ዘይፈጥሩ ።
ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ የሚናገሩትን ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ነገር ፡ እንዳያመጡ ፡ (አለ ፡) ኦሪትን ፡ እንዳያስተምሩ

በዘያስሕቱ ። ሰውን ፡ በሚያስቱ ፡ ገንዘብ ።
ወያመጽኡ ፡ ተኃሥሦ ።
ጾብ ፡ ክርክርን ፡ በሚያመጡ ፡ ገንዘብ ፡ ዘይፈጥሩ ።
ወየኀድጉ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሃይማኖት ።
አንድነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ ትተው ፡ ኢያምጽኡ ፡ ካልአ ።
፭ ፡ ወማኅለቅቱስ ፡ ለትእዛዝ ፡ ተፋቅሮ ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፱ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)

ወያመጽኡ ፡ ተኃሥሦ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የትእዛዝስ ፡ ፍጻሜው ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ልቡና ፡ ኾኖ ፡ ፍቅርን ፡ መያዝ ፡ ነው ።
ወበሠናይ ፡ ግእዝ ።
በበጎው ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ።
ወሃይማኖት ፡ ዘአልቦ ፡ ኑፋቄ ።
መጠርጠር ፡ በሌለበትም ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ፍቅርን ፡ መያዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፮ ፡ እስመቦ ፡ እለ ፡ አውከኩ ፡ ወገብኡ ፡ ውስተ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፰ ።)
ውስተ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ ውስተ ፡ ነገረ ፡ ከንቱ ፡ ይላል ፡ ከወንጌል ፡ ወጥተው ፡ ወደኦሪት ፡ የተመለሱ ፡ አሉና ፡ ከመ ፡ ትገሥጾሙ ።

፯ ፡ ወእንዘ ፡ ይፈቅዱ ፡ መምህራነ ፡ ይኩኑ ፡ ኢያእምሩ ፡ ዘለሊሆሙ ፡ ይነብቡ ፡ (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፬ ፡ ፰ ።)
መምህራን ፡ ሊኾኑ ፡ ሲወዱ ፡ የሚናገሩትን ፡ አያውቁትም ፡ (አለ) ፡ ምሥጢሩን ። አንድም ፡ ንባቡ ፡ ኦሪት ፡ ትርጓሜው ፡ ወንጌል ፡ እንደሆነ ፡ አያውቁትም ።

፰ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ኦሪት ፡ ለዘይገብሮ ፡ በሕጉ ፡ (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።
ኦሪትን ፡ እየነቀፈ ፡ መጥቶ ፡ ነበረና ፡ ኦሪትስ ፡ ሕጉን ፡ ለሚፈጽመው ፡ በሕጉ ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ ደግ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

፱ ፡ ወነአምር ፡ ዘኒ ።
ይህንም ፡ እናውቃለን ፡ (አለ ፡) የሚያመጣውን ።
ከመ ፡ አኮ ፡ ለጻድቃን ፡ ዘይሠራዕ ፡ ሕግ ።
ሕግ ፡ የሚሠራው ፡ ለጻድቃን ፡ እንዳይደለ ።
ዘእንበለ ፡ ለኃጥአን ።
ለኃጥአን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወለጽልሕዋን ። ለከዳተኞች ።
ወለዝሉፋን ።
ኃጢአት ፡ አዘውታሮች ፡ ደፋሮች ፡ ተሳዳቦች ፡ ሴሰኞች ።
ወለውፁዐን ፡ እምጽድቅ ።
ከጽድቅ ፡ ለወጡ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወለርኩሳን ፡ ልብ ።
ልቡናቸው ፡ ድል ፡ ለተነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወቀተልተ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወእሞሙ ።
እናት ፡ አባታቸውን ።
ወቀተልተ ፡ አዝማዲሆሙ ።
ዘመዶቻቸውን ፡ ለማይረዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ብሎ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወቀተልተ ፡ ነፍስ ፡
　　ነፍስ ፡ ለሚገሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትቅትል ፡ ነፍስ ፡ ብሎ ።

፲ ፡ ዘማውያን ።
　　ለሴሰኞች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትዘምው ፡ ብሎ ።

ወእለ ፡ የሐውሩ ፡ ብእሲት ፡ ብእሲ ።
　　ከግብረ ሰዶም ፡ ሚስት ፡ ለሚሔዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትሑር ፡ ኀበ ፡ ብእሲት ፡ ብእሲ ፡ ተብሎ ።

ሰረቅተ ፡ ሰብእ ፡ (ዘፀአ ፡ ፳፩ ፡ ፲፮ ።)
　　ሰውን ፡ እያፈኑ ፡ ለሚሸጡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሰረቅት ፡ የሰውን ፡ ክብት ፡ ለሚሰርቁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢት ስርቅ ፡ ብሎ ።

ሐሳውያን ።
　　(ሰብእ ፡ ሐሳውያን ፡) ሐሰት ፡ ለሚናገሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትኩን ፤ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ብሎ ።

ወእለ ፡ ይምሕሉ ፡ በሐሰት ።
　　በሐሰት ፡ ለሚምሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትጸውዕ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት ፡ ብሎ ።

ወኵ ፡ ባዕድኒ ፡ ዓዲ ፡ ብዘይትቃወሞ ፡ ለትምህርት ፡ ሕይወት ።
　ነጣማለትና ፡ ድኅነት ፡ የሚገኝባትን ፡ ትምህርት ፡ በሚቃወሙ ፡ ሰዎች ፡ የተሠራ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ አለ ።

፲፩ ፡ ዘወንጌለ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለብፁዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአነ ፡ ተአመንኩ ፡ ቦቱ ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፲፭።)
　　ይችውም ፡ እኔ ፡ ያመንሁበት ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌትነት ፡ የሠራት ፡ ወን ጌል ፡ ናት ። አንድም ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚኾን ፡ እኔ ፡ የአመንሁበት ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌትነቱ ፡ የሠ ራት ፡ ድኅነት ፡ የሚገኝባት ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ በሚቃወሙ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የተሠራ ፡ ትእ ዛዝ ፡ አለ ።

፲፪ ፡ እእኵቶ ፡ ለዘተአመነኒ ።
　　ለሐዋርያነት ፡ ትበቃለህ ፡ ያለኝ ።

ወአጽንዐኒ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እግዚእነ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ ገላትያ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።)
　　በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ያጸናኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግነዋለሁ ።

እስመ ፡ ምእመነ ፡ ረሰየኒ ፡ ለመልእክቱ ።
　　ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ ትበቃለህ ፡ ብሎኛልና ።

፲፫ ፡ እንዘ ፡ ቀዲሙ ፡ ፀራፌ ፡ እኅ ፡ ወሰዳዲ ።
　　ምእመናንን ፡ ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ ከአደሩበት ፡ አላውል ፡ የምል ፡ ስኾን ።

ወጸዐሊ ።
　　(ጸራፌ ፡ ወጸዐሊ ፡) ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ የምል ፡ ስኾን ፡ ረሰየኒ ፡ ለመልእክቱ ።

ወባሕቱ ፡ ተሣሀለኒ ።
　　ነገር ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፤ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ እንዘ ፡ ጸራፌ ፡ ወጸዐሊ ።

እስመ ፡ በኢያእምሮ ፡ ገበርኩ ፡ በኢአሚን ።
　　ሳላውቅ ፡ ባለማመን ፡ ሳላምን ፡ ባለማወቁ ፡ አድርጌዋለሁና ።

፲፬ ፡ ወፈድፋደ ፡ ጸጋሁ ፤ ለእግዚአብሔር ፤ በላዕሌየ ።
　　የእግዚአብሔር ፡ ጸጋው ፡ ለኔ ፡ በዝቷልና ።

ወሃይማኖቱ ፡ ወፍቅሩ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ።
　የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅሩ ፡ ሃይማኖቱ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ጸንቷልና ፡ ተሣሃለኒ ።

፲፭ ፡ እሙን ፡ ነገሩ ።
　　ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ።

ወርቱዕ ፡ ይትወከፍዎ ፡ በኵሉ ።
　　በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ሊያምኑት ፡ ይገባል ።

እስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጽአ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለኃጥአን ፤ ዘእኔ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡
(ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩) ።

www.ethiopianorthodox.org

እኔ ፡ ፊታውራሪያቸው ፡ አበጋዛቸው ፡ የምኾን ፡ ኃጥኣንን ፡ ለማዳን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቷልና ፡ እንደመጣ ፡ የተነገረው ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ሊያምኑት ፡ ይገባል ።

፲፮ ፡ ወባሕቱ ፡ ተሣሃለኒ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ ዘእነ ፡ ቀዳሚሆሙ ።

ከመ ፡ ያርኢ ፡ ተአምራቲሁ ፡ በላዕሌየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኔ ፡ ተአምራቱን ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ።

ወብዝኀ ፡ ትዕግሥቱ ።

የትዕግሥቱንም ፡ ብዛት ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ።

ወእኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ ለማግኘት ፡ ለአመኑበት ፡ ሰዎች ፡ አብነት ፡ እኾናቸው ፡ ዘንድ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ ይቅር ፡ አለኝ ፡ እንጂ ፡ ዘእነ ፡ ቀዳሚሆሙ ።

፲፯ ፡ ንጉሥ ፡ ዘለዓለም ።

የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ እንደኾነ ፡ ለሚያምኑበት ፡ (ሐተታ) ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ሲለይ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ አንዱ ፡ ሲያልፍ ፡ አንዱ ፡ ሲተርፍ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ማእከለ ፡ ዓለም ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ።

ዘኢይመውት ።

የማይሸር ፡ ኅልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ።

ወኢያስተርኢ ፡ አምላክ ፡ ባሕቲቱ ።

እሱ ፡ ብቻ ፡ የማይታይ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ።

ዘሎቱ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ክብር ፡ ጌትነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።

አሜን ።	በውነት ።

፲፰ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ አማኅፀንኩከ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ጢሞቴዎስ ።

ልጄ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ሰማይ ፡ ሩቅ ፡ አደራ ፡ ጥብቅ ፡ እንዲሉ ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ።

በከመ ፡ ተነብዮ ፡ ዘላዕሌከ ።

ባንተ ፡ ያለ ፡ መጻእያትን ፡ እንደማወቅህ ፡ አንድም ፡ ትርጓሜን ፡ እንደማወቅህ ፡ መጠን ፡ አማኅፀንኩከ ።

ከመ ፡ ትጽናዕ ፡ በቱሉ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ። (ም ፡ ፯ ፡ ፲፪ ።)

በበጎው ፡ ገድል ፡ ትጸና ፡ ዘንድ ።

፲፱ ፡ እንዘ ፡ ብከ ፡ ሃይማኖት ።

ሃይማኖትን ፡ ይዘህ ።

ወሠናይ ፡ ግዕዝ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፱ ።)

በበጎው ፡ ግብር ፡ ጸንተህ ።

እስመ ፡ ሀለዉ ፡ እለ ፡ አውከኩ ፡ እምሃይማኖት ፡ ወተሰብሩ ።

ከሃይማኖት ፡ ወጥተው ፡ ድል ፡ የተነሡ ፡ አሉና ፡ ወተሰብሩ ፡ ፈቱ ፡ ነገሥት ፡ ሰዶም ፡ በቃለ ፡ ብእሲት ፡ ስብርት ፡ እንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ፡) (ተግ ፡ አሬ ፡ ወር ።)

፳ ፡ እለ ፡ ሂሜኔዎስ ፡	ናቸው ።

ወእለ ፡ እስክንድሮስ ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፲፯ ።)

እሊህ ፡ ናቸው ።

እለ ፡ መጠውክዎሙ ፡ ለሰይጣን ፡ ይትቄነኑ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፭ ።)

ይቀጡ ፡ ዘንድ ፡ ለሰይጣን ፡ አሳልፌ ፡ የሰጠኋቸው ፡ ሲያወግዛቸው ፡ አድሮባቸው ፡ የነበረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይለያቸዋል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከተለያቸው ፡ ማኅደር ፡ ያለኃዳሪ ፡ አይኖርም ፡ ሰይጣን ፡ ያድ ርባቸዋልና ፡ እለ ፡ መጠውክዎሙ ፡ ለሰይጣን ፡ ይትቄነኑ ፡ አለ ።

ኢይልመዱ ፡ ፀሪፈ ።

ክርስቶስን ፡ ሁሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልኒ ፡ ዱቃል ፡ ሕግ ፡ እያሉ ፡ እንዳያስተምሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፡ አስተበቍዐከ ፡ ቀዳሚ ፡ ኵሉ ፡ ትግበር ፡ ጸሎተ ፡ ወስእለ ፡ ወተጋንዮ ፡ (ፊልጵ ፡ ፬ ፡ ፮ ።)
ከሥራው ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጸሎትን ፡ ስዒልን ፡ ተጋንዮን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ
አንድም ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ጸሎትን ፡ ስኢልን ፡ ተጋንዮን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ ፡ አብነት ፡
ነውና ። አንድም ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጸሎትን ፡ ስኢልን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ ፡
ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ነውና ። አንድም ፡ ከኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ ጸሎትን ፡ ስእልን ፡ ተጋንዮን ፡ ታደ
ርግ ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ ። ቀዳሚሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ እማሌቅ ፡ ቀዳሚ ፡ ፍጥረትከ ፡ ብሔሞት ፡ እን
ዲል ፡ ዘኍል ፡ ፳፬ ፡ ፳ ።

፪ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።
ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ጸልዩ ።
ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ነገሥት ።
ለነገሥታቱም ፡ ጸልዩ ።
ወለመኳንንት ።
ለመኳንንቱም ፡ ጸልዩ ፡ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ናቡክደነጾር ፡ ወብልጣሶር ፡ ወልዱ ፡ እንዲል ።
ከመ ፡ በህዱዕ ፡ ወበጽምው ፡ ይኩን ፡ ንብረትነ ፡ በኵሉ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጽሕ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጸንተን ፡ እነዋራችን ፡ በጸጥታ ፡ በዕረፍት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ፡ ኀሡ ፡
ሰላማ ፡ ለብሔር ፡ ከመ ፡ ሰላመ ፡ ዚአሃ ፡ ይኩን ፡ ሰላምክሙ ፡ እንዲል ።

፫ ፡ ዝኬ ፡ ሠናይ ፡ ወኅሩይ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፲) ።
በመድኃኒታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ይህ ፡ ነዋ ።
፬ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይፈቅድ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይሕየው ፡ (ሕዝ ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፱ ።)
ሰው ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ በዕረፍት ፡ ሊኖር ፡ ይወዳልና ፡ ይኩን ፡ ንብረትነ ።
ወያእምርዋ ፡ ለጽድቅ ።
ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ሊያውቋት ፡ ይወዳልና ፡ በኵሉ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጽሕ ።

፭ ፡ እሐዱ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (አለ ፡) በተለየ ፡ አካሉ ። አንድም ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ
በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አሐዱ ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ ሊያውቁ ፡ ይወዳልና ።
ወአሐዱ ፡ ኅሩይ ፡ ማእከለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፳፩ ፡
፳፪ ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬ ።)
ሰው ፡ ኹኖ ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስታረቀ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለ ፡ በተ
ለየ ፡ አካሉ ። አንድም ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ በባሕርይ ፡ በሕልውና ፡ ፩

፮ ፡ ዘመጠወ ፡ ርእሶ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉ ።
ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ የሰጠ ።
ወኮነ ፡ ስማዕተ ፡ በዕድሜሁ ፡ (ገላት ፡ ፩ ፡ ፬ና ፡ ፪ ፡ ፳ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፬) ።
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ። አንድም ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የመሰከረ ፡ አንስ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡
መጻእኩ ፡ ወእንበይነዝ ፡ ተወለድኩ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ሰማዕተ ፡ በጽድቅ ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፴፯ ።)
፯ ፡ ዘሎቱ ፡ ተሠየምኩ ፡ ሐዋርያ ፡ ወዓዋዴ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)
ለሩቁ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለቅርቡ ፡ አስተማሪ ። አንድም ፡ ለብዙው ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ለጥቂቱ ፡ አስተ
ማሪ ፡ የተሾምሁለት ።
እሙን ፡ እብል — እውነት ፡ እናገራለሁ ።
ወኢይሔሱ ። — ሐሰት ፡ አልናገርም ።
ተሠየምኩ ፡ መምህረ ፡ ለአሕዛብ ፡ በሃይማኖት ፡ ወበጽድቅ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጸንቼ ፡ አሕዛብን ፡ ለማስተማር ፡ ተሾሚያለሁና ፡ እንደተሾምሁ ፡ እውነት ፡

www.ethiopianorthodox.org

እናገራለሁ ፣ ሐሰት ፣ አልናገርም ። እንድም ፣ በሃይማኖት ፣ በምግባር ፣ ይጸኑ ፣ ዘንድ ፣ አሕዛብን ፣ ለማ
ስተማር ፣ ተሾሚያለሁና ፣ እውነት ፣ እናገራለሁ ፣ ሐሰት ፣ አልናገርም ።

፰ ፣ ወእፈቅድ ፣ ለኵሉ ፣ ሰብእ ፣ ይጸልዩ ፣ በኵሉ ፣ ገጸ ፣ መካን ።
ሰው ፣ ኹሉ ፣ በአራቱ ፣ መዓዝን ፤ በየጊዜያቱ ፤ በየመዓርጉ ፣ ሊጸልዩ ፣ እወዳለሁ ።
ወያንሥኡ ፣ እደዊሆሙ ፣ በንጹሕ ፣ እንበለ ፣ ነጐርጓር ፣ ወኑፋቄ ።
ያለቂም ፣ ያለጥርጥር ፣ በንጽሕና ፣ ኾነው ፣ እደ ፣ ቃላቸውን ፣ ለጸሎት ፣ እደ ፣ ሥጋቸውን ፣ ለመሥዋ
ዕት ፣ ያነሡ ፣ ዘንድ ፣ እወዳለሁ ።

፱ ፣ ወከማሁ ፣ አንስትኒ ፣ ይትረሰያ ፣ ለጸሎት ፣ በፈሪሀ ፣ እግዚአብሔር ።
ወንዶችን ፣ አሁን ፣ ይጸልዩ ፣ በኵሉ ገጸ ፣ መካን ፣ እንዳልሁ ፣ ሴቶችም ፣ በፈሪሀ ፣ እግዚአብሔር ፣
ኹነው ፣ ለጸሎት ፣ ይጸረሩ ።

ወበኀፍረት ። — ሰውን ፣ በማፈር ፣ ኾነው ።

ወበልቡና ። — በተዘክሮ ፣ እግዚአብሔርም ፣ ኾነው ።

ወበእንጽሖ ፣ ርእሶን ፣ እምዝሙት ።
ሰውነታቸውን ፣ ከዝሙት ፣ በመለየት ፣ ኾነው ፣ ለጸሎት ፣ ይጸረሩ ።
አኮ ፣ በሐብላተ ፣ ወርቅ ።
ይትረሰያ ፣ ብሎ ፣ ነበርና ፣ የወርቅ ፣ እንጥልጥል ፣ በማድረግ ፣ አይደለም ።
ወበባሕርይ ።
ድንቂ ፣ ከሎታ ፣ በማድረግ ፣ አይደለም ።
ወበአልባስ ፣ ቅድው ፣ ዘዕጹብ ፣ ሤጡ ፣ (፩ ፣ ጴጥ ፣ ፫ ፣ ፫ - ፭) ።
ዋጋው ፣ ብዙ ፣ የሚኾን ፣ ያማረ ፣ ልብስ ፣ በመልበስ ፣ አይደለም ።
ወአኮ ፣ በተጸፍሮ ፣ ሥዕርቶን ።
ጠጉራቸውን ፣ ወገሮ ፣ ሥሎሶ ፣ በመሠራት ፣ አይደለም ።

፲ ፣ ዘእንበለ ፣ በዘይደልዎን ፣ ለአንስት ፣ (ም ፣ ፭ ፣ ፲) ።
ለሴቶች ፣ በሚገባ ፣ ግብር ፣ ነው ፣ እንጂ ።
ቀዲሙ ፣ አምልኮ ፣ እግዚአብሔር ፣ በትምህርተ ፣ ጽድቅ ፣ ወበምግባረ ፣ ሠናይ ።
አስቀድሞ ፣ በውነተኛው ፣ ትምህርት ፣ በበጎው ፣ ምግባር ፣ጸንቶ ፣እግዚአብሔርን ፣ማገልገል ፣ነው ፣እንጂ ።
፲፩ ፣ ብእሲት ፣ በጽምው ፣ ትትመሀር ፣ (ኤፌ ፣ ፭ ፣ ፳፪) ።
ሴት ፣ በዝግታ ፣ በጸጥታ ፣ ኹና ፣ ትማር ።
ወትትአዘዝ ፣ በኵሉ ፣ የውሃት ።
በፍጹም ፣ ቅንነት ፣ ኹና ፣ ለባሏ ፣ ትታዘዝ ።

፲፪ ፣ ወብእሲትሰ ፣ ትምህር ፣ ኢናበውሖ ፣ (፩ ፣ ቆሮ ፣ ፲፬ ፣ ፴፬) ።
(ትምህርስ ፣) ልታስተምር ፣ ግን ፣ አናሰናብታትም ።
ወኢትመብል ፣ ላዕለ ፣ ብእሲ ፣ (ዘፍጥ ፣ ፫ ፣ ፲፯) ።
በባሏ ፣ ላይ ፣ እንዳትሠለጥን ፣ አትሠልጥን ።
ዳዕሙ ፣ በጽምው ፣ ተሀሉ ።

በጸጥታ ፣ በዝግታ ፣ ኹና ፣ በመታዘዝ ፣ ትኑር ፣ እንጂ ።
፲፫ ፣ እስመ ፣ አዳም ፣ ቀደመ ፣ ተፈጥሮ ።
አዳም ፣ አስቀድሞ ፣ ተፈጥሯልና ።
ወእምድኅሬሁ ፣ ሔዋን ፣ (ዘፍጥ ፣ ፩ ፣ ፳፯) ።
ከሱ ፣ በኋላ ፣ ሔዋን ፣ ተፈጥራለችና ፣ ኢትመብል ፣ ላዕለ ፣ ብእሲ ።

፲፬ ፣ ወአዳምሰ ፣ ኢስሕተ ፣ አላ ፣ ብእሲት ፣ ስሕተት ፣ ወዐለወት ፣ (ዘፍጥ ፣ ፫ ፣ ፮ ፣ ፪ ፣ ቆሮ ፣ ፲፩ ፣ ፫) ።
ሔዋን ፣ ምክንያተ ፣ ስሕተት ፣ ኾናለች ፣ እንጂ ፣ አዳም ፣ ምክንያተ ፣ ስሕተት ፣ አልኾነምና ፣ ትም
ህር ፣ ኢናበውሖ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰ ፡ ወባሕቱ ፡ ተሐዩ ፡ በእንተ ፡ ውሉዳ ።

ስሕተት ፡ ወዐለወት ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፀልጆቿ ፡ በእመቤታችን ፡ በጌታችን ፡ ከብራለች ።

ለእመ ፡ ነበሩ ፡ በሃይማኖት ፡ ወተፋቅሮ ፡ ወበቅድሳት ።

በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ የጸኑ ፡ ስለኾኑ ።

አንድም ፡ ትምህር ፡ ኢናበውሃ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጆቿን ፡ ሠርታ ፡ ቀጥታ ፡ ብታሳድግ ፡ ትከብራለች ፡ (ለእመ ፡ ነበሩ ፡ በሃይማኖት ፡) በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ የጸኑ ፡ ቢኾኑ ።

ወበአንጽሖ ፡ ርእሶሙ ፡ በአእምሮ ።

በውቀት ፡ በፈሊጥ ፡ ኾነው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ቢኾኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፩ ፡ እሙን ፡ ነገር ።

ነገሩ ፡ ደግ ፡ ነው ።

ዘይፈቅድ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳሰ ፡ ሠናየ ፡ ግብረ ፡ ፈተወ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፳፰) ።

ቅስና ፡ ሊሾም ፡ የወደደ ፡ በጎ ፡ አደረገ ፤ ቢወድ ፡ አይደለም ፡ በቅቶ ፡ ቢገኝ ፡ ነው ።

፪ ፡ ወባሕቱ ፡ ርቱዕ ፡ ይሠየም ፡ ጳጳስ ፡ ዘኢያደሉ ፡ ለገጽ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፪ ፡ ፯) ።

ነገር ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፡ በትምህርት ፡ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ፡ ሊሾም ፡ ይገባል

ዘአልቦ ፡ ምክንያት ።

ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ።

ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ።

ያልደጋገመ ፤ (ድንግል ፡ አይሾም ፡ አላለም

ብእሲ ፡ ንቁህ ።

ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ የነቃ ።

ወጠቢብ ።

ብልሁ ፡ አስተዋይ ።

ወመፍቀሬ ፡ ነግድ ።

እንግዳ ፡ ተቀባይ ።

ዘአንጽሐ ፡ ርእሶ ።

ሰውነቱን ፡ ከኃጢአት ፡ የለየ ።

ወምህር ፡ ወመገሥጽ ።

የሚመክር ፡ የሚያስተምር ። መምህር ፡ ለራሱ ፤ መገሥጽ ፡ ለሌላው ።

፫ ፡ ዘኢያበዝኅ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፰ ፡ ፱ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

(መጠጥ ፡ የማያበዛ) ፡ እይጠጣ ፡ አላለም ።

ዘኢያፈጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ ።

ፈጥኖ ፡ የማይማታ ። አንድም ፡ ፈጥኖ ፡ የማይገዝት ።

ባቍዕ ።

መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ የሚረባ ፡ የሚጠቅም ።

ዘኢይትገዓዝ ።

በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ የማይከራከር ።

ዘኢያፈቅር ፡ ንዋየ ።

ኃላፊውን ፡ ክብት ፡ የማይወድ ።

፬ ፡ ዘሠናይ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤቱ ።

የቤቱ ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነለት ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘቦ ፡ ውሉድ ፡ ዘይትኤዘዙ ፡ በኵሉ ፡ ንጹሕ ፡ (፩ ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)

በንጽሕና ፡ ኹነው ፡ የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ።

ወዘሰ ፡ ኢይክል ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱ ፡ እፎኑ ፡ ያስተሐምም ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

ቤተ ፡ ሰብኡን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ማሳደር ፡ የማይቻለው ፡ ከኾነ ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ያሳድራል ፡ ብለው ፡ እንደምን ፡ ይሾሙታል ፤ ያንድ ፡ ቄስ ፡ ቤተሰቦች ፡ ቢበዙ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ይኾናሉ ፡ እነዚያን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ማሳደር ፡ የማይቻለውን ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ሠርቶ ፡ ቀጥቶ ፡ ያሳድራል ፡ ብለው ፡ ይሾሙታልን ።

ወኢይኩን ፡ ዘእምሐዲስ ፡ ተከለ ።

ከሐዲስ ፡ አማኒ ፡ ወገን ፡ አይሾም ።

ከመ ፡ ኢይትአበይ ።

እንዳይታበይ ፡ ከኔ ፡ በላይ ፡ ቢያጡ ፡ እንጂ ፡ ሾሙኝ ፡ ብሎ ።

ወኢይጸለል ።

በድንቁርና ፡ እንዳይያዝ ።

ወኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ መሥገርተ ፡ ሰይጣን ።

ሰይጣን ፡ በተያዘበት ፡ አሽክለ ፡ እንዳይያዝ ፡ (አለ ፡) ትዕቢት ፡ ነው ።

፯ ፡ ወዓዲ ፡ ርቱዕ ፡ ዘሰብእ ፡ እፍአ ፡ ይንዕድዎ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯) ።

ዳግመኛም ፡ ከምግባር ፡ ከሃይማኖት ፡ በሌላ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የመሰከሩት ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ።

ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ ጽዕለት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫) ።

በስድብ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ማለት ፡ ተንቀፈ ፡ ምእመናን ፡ እንዳይሰደቡ ።

ወመሥገርተ ፡ ሰይጣን ።

ሰይጣን ፡ ሰውን ፡ በሚይዝበት ፡ አሽክላ ፡ እንዳይያዝ ።

፰ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ከማሁ ፡ ንጹሓን ።

ዲያቆናቱም ፡ (ከማሁ ፡) እንደቄሱ ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ።

ወእለትርኢባን ።

በአንድ ፡ ቦታ ፡ የተወሰኑ ፡ አንድም ፡ ሕዋሳታቸውን ፡ የሰበሰቡ ፡ ይኹኑ ።

እለ ፡ እሐዱ ፡ ቃሎሙ ።

ሳንዱ ፡ አንድ ፡ ሳንዱ ፡ አንድ ፡ ጡት ፡ አንድ ፡ ማታ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ ነገር ፡ የማይለዋወጡ ፡ ይኹኑ ።

እለ ፡ ኢያበዝኁ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ።

መጠጥ ፡ የማያበዙ ፡ ይኹኑ ፡ አይጠጡ ፡ አላለም ።

እለ ፡ ኢያፈቅሩ ፡ ረባሐ ፡ ከንቶ ፡ (ሬልቅ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፫) ።

ኃላፊውን ፡ ገንዘብ ፡ የማይወዱ ፡ ይኹኑ ።

፱ ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡ ምክረ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ በልብ ፡ ንጹሕ ።

ከክህደት ፡ ከኑፋቄ ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ልቡና ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ትምህርት ፡ አጽንተው ፡ የያዙ ፡ ይኹኑ ።

፲ ፡ ወሎሙኒ ፡ ይቅድሙ ፡ አመክሮቶሙ ።

እሊያን ፡ ቅሉ ፡ አስቀድመው ፡ ይፈትኗቸው ።

ወእምዝ ፡ ይትለአኩ ፡ እምከመ ፡ ኀሩያን ፡ እሙንቱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በቅተው ፡ ቢገኙ ፡ ይሾሙ ።

፲፩ ፡ ወልንስቲሆን ፡ ከማሁ ፡ እለ ፡ እንጽሐ ፡ ርእሶን ፡ (ሮሜ ፡ ፲ ፡ [illegible]) ።

እሁን ፡ ወንዶችን ፡ ዲያቆናት ፡ ንጹሓን ፡ ይኹኑ ፡ እንዳልሁ ፡ ዲያቆናውያት ፡ ሴቶችም ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከኃጢአት ፡ የለዩ ፡ ይኹኑ ።

እለ ፡ ተምህሩ ፡ ሥርዓተ ።

ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የተማሩ ።

እለ ፡ ኢያስተዳኅጻ ።

ነገር ፡ ሠርተው ፡ እንዱን ፡ ከእንዱ ፡ የማያጣሉ ፡ ይኹኑ ።

ጠባባት ። ብልሆች ።

www.ethiopianorthodox.org

ራትዓት ። ቅኖች ፡ ይኹን።

ወምእመናት ፡ በኵሉ ።

በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ የታመኑ ፡ ይኹኑ ፡፡

ወይትለአካ ።

(ይትለአካ ፡) እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ይሾሙ ።

፲፪ ፡ ወብእሲኒ ፡ ዘእሐቲ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ

የቄሱን ፡ ተናገሮ ፡ የዲያቆኑን ፡ አልተናገረውም ፡ ነበርና ፡ ዲያቆንም ፡ ያልደጋገመ ፡ ይሾም ፡ ድንግል ፡ አይሾም ፡ አላለም ።

ዘበ ፡ ውሉድ ።

የተሠሩ ፡ የተቀጡ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ።

ዘሠናይ ፡ ግዕዘ ፡ ቤቱ ፡ (ቍ ፡ ፪ ።)

የቤቱ ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነለት ።

፲፫ ፡ ወአለሰ ፡ ሠናየ ፡ ይትለአኩ ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሢመተ ፡ ይግበሩ ፡ሎሙ ፡ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳፩) ።

(ሎሙ ፡ ለአለ ፡ ይትለአኩ ፡) በጎ ፡ ማገልገልን ፡ ላገለገሉ ፡ ዲያቆናት ፡ የበለጠ ፡ ያደርጉላቸው ፡ (እለ) ፡ ከዲቁና ፡ ወደቅስና ፡ ከቅስና ፡ ወደኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ያውጧቸው ።

በብዙኅ ፡ ሞገስ ፡ በሃይማኖተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፳ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፳፭ ።)

በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምነ ፡ የሚሾሙት ፡ ብዙ ፡ መዓርግ ፡ ሀብት ፡ አለና ፡ እንተ ፡ ተዐቢ ፡ ሢመተ ፡ ይግበሩ ፡ ሎሙ ። አንድም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምነ ፡ የሚሠሩት ፡ ብዙ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ አለና ፡ ይቅድሙ ፡ አመክሮቶሙ ፡ እምኵሉ ፡ ኅሩያን ፡ እሙንቱ ።

፲፬ ፡ ወዘኒ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ለከ ፡ እትአመን ፡ ከመ ፡ እበጽሐከ ፡ ፍጡነ ።

ይህንም ፡ ስጽፍልህ ፡ ፈጥኜ ፡ ወደአንተ ፡ እንድመጣ ፡ አምናለሁና ።

፲፭ ፡ ወአመሰ ፡ ጐንደይኩ ፡ ከመ ፡ ታእምር ፡ ዘከመ ፡ ትሠርዕ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡

(፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳ ።)

ፈጥኜ ፡ ባልመጣ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑ ፡ ምእመናንን ፡ ሠርተህ ፡ ቀጥተህ ፡ እንድታሳድር ፡ የምታሳድርበትን ፡ ሥርዓት ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዐምዳ ፡ ወድዳ ፡ ለጽድቅ ።

የሃይማኖት ፡ ጽንዕ ፡ መሠረት ፡ የሚኾን ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀጠለ ፡ አንድም ፡ የሃይማኖት ፡ ጽንዕ ፡ መሠረት ፡ የምትኾን ፡ ብሎ ፡ ለምእመን ፡ ቀጠለ ፡ አንድም ፡ ለሥርዓቱ ፡ ቀጠለ ።

፲፮ ፡ አማን ፡ ዐቢይ ፡ እስመ ፡ ምክሩ ፡ ለዝንቱ ፡ ጽድቅ ፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።)

የዚህ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገሩ ፡ (እስመ ፡ ዐቢይ ፡) ደግ ፡ እንደመኾኑ ፡ (አማን ፡ ጽድቅ ፡) እውነት ፡ ነው ። አንድም ፡ የዚህ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገሩ ፡ (እስመ ፡ ጽድቅ ፡) እውነት ፡ እንደመኾኑ ፡ (አማን ፡ ዐቢይ ፡) ፡ ደግ ፡ ነው ፤ ደግ ፡ ነው ፡ እኮ ።

ዝኬ ፡ ዘአስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ሰብአ ።

ይኸውም ፡ በሥጋ ፡ የታየው ፡ መታየት ፡ ነው ።

ወጸድቀ ፡ በመንፈስ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፲ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፬ ።)

በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተረዳነው ፡ መረዳት ፡ ነው ።

ወአስተርአዮሙ ፡ ለመላእክት ።

አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ያልኸው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትሉኝ ፡ እን ደኾነ ፡ በዕለተ ፡ ልደት ፡ ለመላእክት ፡ ታያቸው ።

ወሰበክዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።

ለኖሎት ፡ ነገሯቸው ። አንድም ፡ ለኖሎት ፡ ታያቸው ፡ ለአይሁድ ፡ ነገሯቸው ።

አንድም ፡ ወአስተርአዮሙ ፡ ለመላእክት ።

በዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ለመላእክት ፡ ታያቸው ።

ወሰበክዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ።

ለአንስት ፡ ነገሯቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

እንድም ፡ ወአስተርአየሙ ፡ መላእከት ፡፡
ለእንስታት ፡ ታያቸው ፡፡
ወሰበከዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ፡፡
ለሐዋርያት ፡ ነገራቸው ፡፡
እንድም ፡ ወአስተርአየሙ ፡ ለመላእክት ፡፡
ለሐዋርያት ፡ ታያቸው ፡፡
ወሰበከዎ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ፡፡
ለአሕዛብ ፡ አስተማራቸው ፡፡
ወተአምነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡፡
በዓለሙ ፡ ዘንድ ፡ ታመነ ፡ ተረዳ ፡፡
ወዐረገ ፡ በስብሐት ፡ (ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡፡)
በብርሃን ፡ በሥልጣን ፡ ብቅዳሴ ፡ ባረገ ፡ ጊዜ ፡ ታመነ ፡ ተረዳ ፡፡

ምዕራፍ ፡ ፬ ፡፡

ወመንፈስ ፡ ገሃደ ፡ ይነግር ፡ ከመ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ የዐልዉ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ብዙኃን ፡ (ዳን ፡ ፯ ፡ ፳፭ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ የሐ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ይሁ ፡ ፲፰ ፡፡)
ወተአምነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኔ ፡ አድሮ ፡ ገልጦ ፡ ይናገራል ፡፡
ወይትልውዎሙ ፡ ለአጋንንት ፡ እኩያን ፡ ወመስሕታን ፡
እኩያን ፡ መስሕታን ፡ አጋንንትን ፡ እንዲመስሏቸው ፡፡
ወትምህርተ ፡ ሰይጣን ፡ ዘያናፍቅ ፡፡
የሚያጠራጥር ፡ የሰይጣንን ፡ ትምህርት ፡ እንዲይዙ ፡ ይነግር ፡፡

፫ ንዓብያን ፡ ሐስት ፡፡
ሐሰትን ፡ እንዲቀባጥሩ ፡፡
እለ ፡ ንዱዳን ፡ በሕሊናሆሙ ፡ እለ ፡ የኀርሙ ፡ አውስቦ ፡፡
ግቢ ፡ ርኩስ ፡ እያሉ ፡ በፈቲው ፡ ጾር ፡ የሚናደዱ ፡ እንዲኾኑ ፡ እንዲናደዱ ፡፡
ወይከልኡ ፡ መባልዕተ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ፈጠረ ፡ ለምእመናን ፡ (ዘፍጥ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡፡)
እግዚአብሔር ፡ ለምእመናን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ ሥጋ ፡ ፍጥረት ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ፡ ርኩስ ፡ የሚሉ ፡፡
ከመ ፡ ይሴሰዩ ፡ ወያእኩቱ ፡ እለ ፡ ያእምርዋ ፡ ለጽድቅ ፡ (፩ ፡ ቆር ፡ ፲ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ፡፡)
ሃይማኖትን ፡ የሚያውቋት ፡ ሰዎች ፡ በልተው ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡፡

፬ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ተግባረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡፡
እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ፡፡ ወርአየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ እንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ፡ ፳፭ ፡፡)
ወእልቦ ፡ ግዱፍ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ለአመ ፡ ተወከፍዎ ፡ እንዘ ፡ ያእኩቱ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፲፭ ፡፡)
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርተው ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግመው ፡ እምና ፡ ቢመገቡት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚጣል ፡ የለምና ፡ (እለ ፡) ርኩስ ፡ የለምና ፡ ይሴሰዩ ፡ ወያእኩቱ ፡፡

፭ ፡ እስመ ፡ ይትቄደስ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበጸሎት ፡፡
ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደግሞ ፡ ቢበሉት ፡ የሚከብር ፡ ስለኾነ ፡፡

፮ ፡ ወዘንተ ፡ መሀሮሙ ፡ ለአኃዊከ ፡፡
ለወንድሞችህ ፡ ይህን ፡ አስተምራቸው ፡፡
ወትከውን ፡ ኄሩየ ፡ ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡፡)
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግ ፡ አገልጋይ ፡ ትኾናለህ ፡፡ እንድም ፡ ላእከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ (ትከውን ፡ ኄሩየ) ፡ ደግ ፡ ትባላለህ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዘ ፡ ትሴስዮሙ ፡ ቃለ ፡ ሃይማኖት ።
የሃይማኖትን ፡ ነገር ።
ወሠናየ ፡ ትምህርተ ፡ ዘተመሀርከ ።
ከኔ ፡ የተማርኸውን ፡ ትምህርት ፡ ስታስተምራቸው ፡ ብትገኝ ፡ ትከውን ፡ ኄሩየ ።

፯ ፡ ወስመሐድምተ ፡ ዕቤራትስ ፡ ርኩስ ፡ ዕበዮ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፬ና ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪፡፲፯፡፳፫፡ቲቶ፡፩፡፲፬ና፫፡፱።)
ርኩሳን ፡ ቢል ፡ ለዕቤራት ፤ ርኩስ ፡ ቢል ፡ ለመሐድምት ፡ ይቀጥላል ፡ የባልቴቶች ፡ ተረት ፡ አራትም ፡
ግን ፡ ተወው ።
ወአግርር ፡ ርእሰከ ፡ ለጽድቅ ።
ለጽድቅ ፡ ለወንጌል ፡ ቀግዛ ።

፰ ፡ እስመ ፡ ግዝረትሰ ፡ በሥጋ ፡ ለኀዳጥ ፡ ዘመን ፡ ትበቍዕ ፡ በ ፡ (ም ፡ ፯ ፡ ፯ ።)
ለአራት ፡ መገዛት ፡ ለሥጋ ፡ መጥቀሙ ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፡ ዕበዮ ።
ወጽድቅሰ ፡ ታሠልጥ ፡ በኵሉ ።

ጽድቅ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ነውና ፡ አግርር ፡ ርእሰከ ፡ እንድም ፡ ለአራት ፡ መገዛት ፡ ለጥ
ቂት ፡ ዘመን ፡ በሥጋ ፡ ይጠቅማልና ፡ ዕበዮ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌል ፡ ግን ፡ በሥጋም ፡ በነፍስም ፡ ትጠቅማለ
ችና ፡ አግርር ፡ ርእሰከ ።
ወባቲ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወት ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፤ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የድኅነት ፡ እለኝታ ፡ ይገኝባታል ።

፱ ፡ እሙን ፡ ነገሩ ፡ ወርቱዕ ፡ ይትወከፍዎ ፡ በኵሉ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፭ ።)
ነገሩ ፡ ደግ ፡ ነው ፤ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ሊያምኑት ፡ ይገባል ።

፲ ፡ እስመ ፡ በእንተዝ ፡ ንሠርሕ ፡ ወንጼዓል ።
ስለዚህ ፡ በመከራው ፡ እንደክማለንና ፤ እንዋረዳለንና ።
እስመ ፡ ተወከልነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ መግሕየዊ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ።)
ሕያው ፡ ማሕየዊ ፡ በሚኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስለአመነ ።(ሐተታ) ፡ ሕያው ፡ ስራሱ ፡ ማሕየዊ ፡ ለሌላው ።
ወፈድፈደሰ ፡ ለመሃይምናን ፡ (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳፫) ።

ይልቁንም ፡ ማሕየዊነቱ ፡ ለምእመናን ፡ ነው ፡ በሥራ ፡ ያስፋፋታልና ።
ከመዝ ፡ መሀር ፡ ወገሥጽ ።
እንዲህ ፡ ምከር ፡ አስተምር ።

፲፩ ፡ ወአልቦ ፡ ዘያስተአብዳ ፡ ለውርዙትከ ፡ (ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፭) ።
የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ሕፃንነትህን ፡ የሚነቅፋት ፡ አይኑር ፡ ሕፃን ፡ እንጂ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ ብሎ ፤
እንድም ፡ ሕፃን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካንተ ፡ በፊት ፡ የሚጸልይ ፡ አይኑር ።
ወኩኖሙ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለምእመናን ፡ በቃልከ ፡ ወበምግባርከ ፡ በፍቅር ፡ ወበሃይማኖት ፡ ወበንጽሕ ።
በሃይማኖት ፡ በፍቅር ፡ በንጽሕና ፡ ጸንተህ ፡ በምትናገረው ፡ ነገር ፡ በምትሠራው ፡ ሥራ ፡ ለምእመናን ፡
አብነት ፡ ኹናቸው ።

፲፫ ፡ ወተዐቀብ ፡ እስከ ፡ እመጽእ ፡ በአንብቦ ።
እስከመጣ ፡ ድረስ ፡ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ተወስነህ ፡ ኑር ።
ወበምሂር ፡ ወበገሥጽ ፡ ወበጸልዮ ፡ (ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፴፱) ።
በምክር ፤ በማስተማር ፤ በጸሎት ፡ ተወስነህ ፡ ኑር ።

፲፬ ፡ ወኢታስትት ፡ ጸጋሁ ፡ ዘላዕሌከ ፡ ዘተውህበከ ፡ ምስለ ፡ ተነብዮ ።
ትርጓሜን ፡ መጸእያትን ፡ ከማወቅ ፡ ጋራ ፡ የተሰጠህን ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።
ወምስለ ፡ ሢመተ ፡ እዴሆሙ ፡ ለጳጳሳት ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፳፪ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፮ ፡ ፮ና ፡ ፰ ፡ ፲፯ ።)
ቀሳውስትን ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ከመሾም ፡ ጋራ ፡ የተሰጠህን ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል። እንድም፡
ቀሳውስት ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ከሚሾሙት ፡ ሹመት ፡ ጋራ ፡ የሰጠህን ፡ ሀብት ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።

፲፭ ፡ ዘንተ ፡ አንብብ ።
ይህን ፡ አስተውል ።

www.ethiopianorthodox.org

ወበዝ ፡ ሀሉ ። ብዚህ ፡ ጸንተሀ ፡ ኑር ።
ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ምላጤከ ፡ በኵሉ ፡ ።
ፍጹምነትህ ፡ በሁሉ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ።

፲፮ ፡ ዑቅ ፡ እንከ ፡ ርእሰከ ፡ በእንተ ፡ እንብቦ ።
መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ተወስነህ ፡ እንድትኖር ፡ ዕወቅ ።
ወዘልፈ ፡ ሀሉ ፡ ባቲ ።
በዚያው ፡ ጸንተሀ ፡ እንድትኖር ፡ ዕወቅ ።
ወእመሰ ፡ ዘንተ ፡ ገበርከ ፡ ርእሰከኒ ፡ ታድኅን ።
ይህን ፡ ያደረግህ ፡ እንደኾነ ፡ ራስህን ፡ ታድናለህ ።
ወዘሂ ፡ ይሰምዐከ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፲፬) ።
የሚሰማህንም ፡ ታድናለህ ። እንድም ፡ የምታስተምረውን ፡ ብትሠራው ፡ ራስህንም ፡ ሌላውንም ፡ ታድ
ናለህ ፡ ለእመሂ ፡ ሰምዑከ ፡ አድኃንከ ፡ ሕዝበከ ፡ ወለእመሂ ፡ ኢሰምዑከ ፡ አድኃንከ ፡ ርእሰከ ፡ ያለውን ፡
ሕዝቅኤል ፡ እንዲህ ፡ ለውጦ ፡ አነበበው ። (ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፰) ።

●○○○●

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ ሊቃናተ ፡ ኢታመጕጽ ፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፴፪።)
ሽማግሎችን ፡ አትንጠብ ፡ (አለ ፡) አታዋርድ ፡ አትናቅ ፡ አታቃል ።
ተአዘዝ ፡ ከመ ፡ ዘለአቡከ ።
ለአባትህ ፡ እንድምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለንኡሳን ፡ ከመ ፡ ዝለአኀዊከ ።
ለሕፃናቱም ፡ ወንዶች ፡ ለወንድሞችህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለልሂቃትኒ ፡ ከመ ፡ ዘለእምከ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯) ።
ለባልቴቶችም ፡ ለናትህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዝ ፡ እንጂ ።
ወለንኡሳትኒ ፡ ከመ ፡ ዘለአኃቲከ ፡ በኵሉ ፡ ንጹሕ ።
ለሕፃናቱም ፡ ሴቶች ፡ ለእኅቶችህ ፡ እንደምትታዘዝ ፡ ታዘዛቸው ፡ (በኵሉ ፡ ንጽሕ ፡) በንጽሕና ፡ ኾነህ ፤
ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ዝሙት ፡ ይቀዋወማቸዋልና ፡ ንጽሕን ፡ ያቆራኛል ።

፫ ፡ ወአክብር ፡ ዕቤራተ ፡ በጽድቅ ፡ (ቍ ፡ ፭) ።
(አክብር ፡ በጽድቅ ፤ ዕቤራተ ፡ በጽድቅ ፡) በውነት ፡ እረጅ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸው ፡ ባልቴቶችንም ፡ በእው
ነት ፡ እርዳ ።

፬ ፡ ወእመቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዕቤር ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ውሉድ ።
ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ልጆች ፡ ያሏት ፡ ድኃ ፡ ባልቴት ፡ ብትኖር ።
አው ፡ ደቂቀ ፡ ውሉድ ።
የልጅ ፡ ልጅ ፡ ያላት ፡ ብትኖር ።
ይትመሀሩ ፡ ቅድመ ፡ አሠንዮ ፡ ለቤቶሙ ።
ውሉድ ፤ እናት ፡ አባታቸውን ፡ ይረዱ ።
ወይሴስዩ ፡ አዝማዲሆሙ ።
ደቂቀ ፡ ውሉድ ፤ እያቶቻቸውን ፡ ይርዱ ።
እስመ ፡ ከማሁ ፡ ሠናይ ፡ ወሥሙር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር
ይህ ፡ እናት ፡ አባትን ፡ መርዳት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

፭ ፡ ወእንተሰ ፡ ዕቤር ፡ በአማን ፡ ንጽሕት ፡ እንተ ፡ ባሕቲታ ፡ ትነብር ፡ በውነት ፡ እረጅ ፡ ልጅ ፡ የሌላት ፡ ብቻ
ዋን ፡ በንጽሕና ፡ የምትኖር ፡ ባልቴቲቱን ፡ ግን ።
እስመ ፡ ትውከልታ ፡ እግዚአብሔር ።
ተስፋዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

ወትፀመድ ፡ ጸሎተ ፡ ወትስእል ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ (ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፯ ፡ ፲፰ ፡ ፩) ።
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በጸሎት ፡ ፅሙድ ፡ ኾና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትለምነዋለችና ፡ ርዳት ።

፮ ፡ ወእንተሰ ፡ ትፌግዕ ፡ ምስለ ፡ ተውኔት ፡ ምውት ፡ ይእቲ ፡ እንዘ ፡ ሕያዋ ፡ (ሮሜ ፡ ፰፡ ፲፫ ።)
በዘፈን ፡ በጨዋታ ፡ እየኖረች ፡ተድላ ፡ ደስታ ፡ የምታደርገውን ፡ ግን ፡ በወዲሁ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡
ስትል ፡ በወዲያው ፡ ምውት ፡ ናትና ፡ አትርዳት ።
ወከመዝ ፡ ገሥጽ ።
እንዲህ ፡ ምክር ፡ አስተምር ።
ከመ ፡ ኢየድልዉ ፡ ወኢያመክንዩ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲፩) ።
ዘፈኗን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ እንዳያዳሉላት ።

፰ ፡ ወዘሰ ፡ ኢይሔሊ ፡ ለቤቱ ፡ (ገላትያ ፡ ፮ ፡ ፲) ።
እናት ፡ አባቱን ፡ የማይረዳ ።
ወይገድፍ ፡ አዝማዲሁ ።
እያቶቹን ፡ የማይረዳ ።
ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ እምሰብአ ፡ ሃይማኖት ።
ይልቁንም ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ቢኾኑ ።
ውእቱ ፡ ክህደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ (ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፭) ።
እሱ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ካደ ።
ወየአኪ ፡ እምዘ ፡ ኢየአምን ።
ከኢአማኒም ፡ ይከፋል ።

፱ ፡ ወለእመ ፡ ኀረይከ ፡ ዕቤረ ፡ ኅረይ ፡ እንተ ፡ ሰሳ ፡ ክረምታ ።
ዲያቆናዊት ፡ ልትሾም ፡ ብትወድ ፡ ፷ ፡ ዘመን ፡ የመላትን ፡ ደም ፡ የቀረጠችውን ፡ መርጠህ ፡ ሹም ።
እንተ ፡ ፩ደ ፡ ብእሴ ፡ አውሰበት ።
ያልደጋገመችውን ።

፲ ፡ እንተ ፡ ይንዕድዋ ፡ በኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።
በበጎው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የሚያመሰግኗትን ።
ለእመ ፡ አልሀቀት ፡ ውሉዳ ።
ልጆቿን ፡ ሠርታ ፡ ቀጥታ ፡ ብታሳድግ ።
ወለእመ ፡ ነግደ ፡ ተወክፈት ፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፪) ።
እንግዳ ፡ ብትቀበል ።
ወለእመ ፡ እግረ ፡ ጸድቃን ፡ ኀፀበት ።
የድሆችን ፡ እግር ፡ ብታጥብ ፡ የሚያመሰግኗትን ። ዝራዕ ፡ እክለከ ፡ ላዕለ ፡ መቃብረ ፡ ጻድቃን ፡ ጠቢት ፡
(፭ ፡ ፲፯) ፡ እደው ፡ ጻድቃን ፡ የሀልዉ ፡ ውስተ ፡ ምሳሕከ ፡ እንዲል ፡ (ሲራ ፡ ፱ ፡ ፳፫) ፡
ወእመ ፡ ርኁበ ፡ አጽገበት ።
የተራበ ፡ ብታበላ ፡ የሚያመሰግኗትን ።
ወኵሎ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ለእመ ፡ ተለወት ።
ነግግለትና ፡ በጎውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አጽንታ ፡ ብትይዝ ፡ የሚያመሰግኗትን ፡ መርጠህ ፡ ሹም ።

፲፩ ፡ ወለንኡሳትሰ ፡ መበለታት ፡ ተገኃሥን ።
ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ግን ፡ ተለያቸው ።
ወኢትሢሞን ።
አትሹማቸው ።
ከመ ፡ ኢይትፈግዓ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይፈቅዳ ፡ ይግብአ ፡ ለአውስቦ ።
ተመልሰው ፡ ባል ፡ ሊያገቡ ፡ ወደው ፡ በክርስቶስ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳያደርጉበት ።

፲፪ ፡ ወጽኑሕ ፡ ደይናን ።
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ ፍዳቸው ፡ ይቆያቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለእመ ፡ ክህዳ ፡ ሃይማኖቶን ፡ ቀዳሚተ ።
    የቀደመ ፡ ብፅዓታቸውን ፡ ቢያፈርሱ ፡ ጽኑሕ ፡ ደይናን ።

፲፫ ፡ ወዓዲ ፡ አጽርዕተ ፡ ወሐኬተ ፡ ይትሜሐራ ፡ እንዘ ፡ የዓውዳ ፡ አብያተ ፡ (ምሳ ፡ ፯ ፡ ፲፩) ።
    በዚህም ፡ ላይ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ እየዞሩ ፡ አጽርዕትን ፡ ሐኬትን ፡ ይማራሉ ፡ (አጽርዕት) ፡ እግር ፡
    ዝርጊት ፡ (ሐኬት ፡) በወር ፡ ጥልቅ ፡ በዓመት ፡ ቀሚስ ፡ ጥልቅ ።
ወአኮ ፡ አጽርዕተ ፡ ባሕቲቶ ።
    መንደር ፡ ለመንደር ፡ መዞራቸውም ፡ አጽርዕትን ፡ ሐኬትን ፡ ለመማር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
አላ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ያብዝኃ ፡ ነቢበ ።
    አብዝተው ፡ ለመቀባጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወምግባረ ፡ ከንቱ ።
    ከንቱ ፡ ሥራንም ፡ ለመሥራት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ይፈጥራ ፡ ነገረ ፡ ዘኢህልዉ ።
    ቀዋሚ ፡ ያይደለ ፡ ነገር ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ።

፲፬ ፡ እፈቅድ ፡ እንከ ፡ ለንኡሳት ፡ ያውስባ ፡ ወይትዋለዳ ፡ ወይኩና ፡ በዓልታተ ፡ ቤት ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፱) ።
    እኔስ ፡ ሕፃናቱ ፡ ሴቶች ፡ ባል ፡ አግብተው ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገዝተው ፡ ሊኖሩ ፡ እወዳለሁ።
ወኢይርከብ ፡ ምክንያተ ፡ ወእሐተኒ ፡ በዘይጸብአን ፡ ጸላዒ ።
    ጸላዒ ፡ ዲያብሎስ ፡ ድል ፡ በሚነሣቸው ፡ ገንዘብ ፡ ድል ፡ የሚነሣበት ፡ ምክንያት ፡ እንዳያገኝ ።
ከመ ፡ ኢያጽዕላ ፡ ርእሶን ።
    ራሳቸውን ፡ እንዳያስነቅፉ ፡ አንድም ፡ ራሳቸውን ፡ ክርስቶስን ፡ እንዳያስነቅፉ ፡ ንሕነ ፡ አባል ፡ ወውእቱ ፡
    ርእስ ፡ እንዲል ።

፲፭ ፡ እስመቦ ፡ እለ ፡ ተመይጡ ፡ ወተለውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፮) ።
    ተመልሰው ፡ የሰይጣንን ፡ ግብር ፡ የያዙ ፡ አሉና ፡ ኢያጽዕላ ።

፲፮ ፡ ወለእመ ፡ ቦ ፡ እምእመናን ፡ ዘቦ ፡ ዕቤር ፡ ይዕቀባ ።
    ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ደኃ ፡ እናት ፡ ያለችው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይርዳት ።
ወኢያክብድ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።
    ምእመናንን ፡ እንዳያስቸግር ፡ እንዳታስቸግር ።
ከመ ፡ ትክሀል ፡ ለእለ ፡ በአማን ፡ ዕቤራት ።
    ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ ረጅ ፡ ልጅ ፡ የሌላቸውን ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ እለ ፡ ሠናየ ፡ ተልእኩ ፡ ቀሲሳን ፡ ምክዕቢተ ፡ ይደልዎሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፱ ፡ ፳፯ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮) ።
    በጎ ፡ ማገልገልን ፡ ሳገለገሉ ፡ ቀሳውስት ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ።
ወፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ ይሰርሑ ፡ በቃል ፡ ወበምህሮ ።
    ይልቁንም ፡ (በቃል) ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ የሰሙትን ፡ (ወበምህሮ) ፡ ከመጽሐፍ ፡ ያገኙትን ፡ በማስተማር ፡
    ለሚደክሙ ፡ መምህራን ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ።

፲፰ ፡ ወይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ኢትፍጽሞ ፡ አፉሁ ፡ ለላህም ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ አክለከ ፡ (ዘዳግ ፡ ፳፭ ፡ ፬፡፩፡ቆሮ፡፲፱፡፱)
    እህልህን ፡ በምታሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የላምህን ፡ አፉን ፡ እትሰረው ፡ ብሏልና ።
ወይደልዎ ፡ እስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፯) ።
    ይደልዎ ፡ እስቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ብሏልና ፡ (ምክዕቢተ ፡ ክብር ፡ ይደልዎሙ ፡) (ሐተታ) ከእፃዌ ፡ ሞኅት
    ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሽቅብ ፡ እየሰጠ ፡ ይሔዳል ፡ በኹለተኛው ፡ ከዲያቆን ፡ ጀምሮ ፡ ይሰጣል፤
    በሦስተኛው ፡ ከቄስ ፡ ይጀምራል ፤ ባራተኛው ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ስጦቶ ፡ ይመለሳል ፡ አንድም ፡ ከኤጲስ
    ቆጶሱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እፃዌ ፡ ሞኅት ፡ እየሰጠ ፡ ይወርዳል ፡ በኹለተኛው ፡ ለዲያቆን ፡ ስጦቶ ፡ ይመለሳል
    በሦስተኛው ፡ ለቄስ ፡ በአራተኛው ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ሰጥቶ ፡ ይመለሳል ፡ አንድም ፡ አራቱን ፡ ከአንድ
    ላይ ፡ ሦስቱን ፡ ከአንድ ፡ ላይ ፡ ኹለቱን ፡ ከአንድ ፡ ላይ ፡ አንዳንዱን ፡ በየራሱ ፡ አድርጎ ፡ በየገንዘባችሁ፡
    አንሡ ፡ ይላቸዋል ፡ ያነሣሉ ።

፲፱ ፡ ላዕለ ፡ ልሂቅ ፡ ኢትስማዕ ፡ ውዴተ ።
    በቄሱ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡ አትስማበት ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘእንበለ ፡ ይዝልፍዎ ፡ ክልኤቱ ፡ ወሠለስቱ ፡ ሰማዕት ፡(ዮሐ ፡፰ ፡፲፯ ።)
ኹለት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ሳይመሰክሩበት ።

፳ ፡ ወለእለሂ ፡ ስሕቱ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ገሥጾሙ ፡ (ኤፌ፡ ፭ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ።)
ስሕቱ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ገሥጾሙ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡) በጉባኤ ፡ የበደሉትንም ፡ በጉባኤ ፡ ገሥጻቸው
ከመ ፡ ባዕድኒ ፡ ይፍራህ ።
ሌላው ፡ ፈርቶ ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ፡ ዝሉፍ ፡ እንዘ ፡ ይትጌሠጽ ፡ አብድ ፡ ይከውን ፡ ማዕምረ ፡ እንዲል ።

፳፩ ፡ እሰምዕ ፡ ለከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አዳኝብሃለሁ ።
ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ።
ወበመላእክቲሁ ፡ ኅሩያን ።
በመላእክትም ፡ ፊት ፡ እዳኝብሃለሁ ።
ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ኢታደሉ ።
በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፡ በትምህርት ፡ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይተህ ፡ ሳታደላ ፡ ይህን ፡ ትጠብቅ ዘንድ ፡ አዳኝብሃለሁ ።
ወኢታጽድቆ ፡ ለሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ፍትህ
ሳይመሰክርበት ፡ እንዳያደርግ ፡ ዐውቃለሁ ፡ አትበል ።
ወኢትግበር ፡ ምንተሂ ፡ በዘትትሔመይ ።
በምትነቀፍ ፡ ገንዘብ ፡ የምትነቀፍበትን ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡እንጂ ፡ ሰምቶ ፡ ቃል ፡ ለቃል ተጨዋውቶ ፡ ይሉታልና ።
ወኢታጽድቆ ፡ ለሰብእ ፡ ቅድመ ፡ ፍትሕ ።
(አንድም) ፡ሳይመሰክርለት ፡ እንዳያደርግ ፡ ዐውቃለሁ ፡ አትበል ።
ወኢትግበር ፡ ምንተሂ ፡ በዘትትሔመይ ።
በምትነቀፍ ፡ ገንዘብ ፡ የምትነቀፍበትን ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፡ መማለጃ ፡ በልቶ ፡ ተዘምዶ ፡ ሥጋ ኑሮት አድልቶ ፡ ይሉታልና ።
፳፪ ፡ ወኢትሢም ፡ ፍጡነ ፡ ወኢመነሂ ፡(ግብ ፡ሐዋ፡ ፮፡ ፯ ።)
ማንንም ፡ ማን ፡ ሳትመረምር ፡ ፈጥነህ ፡ አትሹም ።
ወኢትሳተፍ ፡ በገ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአተ ፡ ባዕድ ።
በዚህ ፡ ሌላው ፡ በሠራው ፡ ኃጢአት ፡ አንት ፡ በፍዳ ፡ እንዳትያዝ ፡ እኩ ፡ ዘገብረ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘይትኴነኝ እላ ፡ ዘሂ ፡ ሠምረ ፡ በኃጢአተ ፡ ዝኩ ፡ እንዲል ።
ወአንጽሕ ፡ እንከ ፡ ርእሰከ ።
ሰውነትህን ፡ ከኃጢአት ፡ ለይ ።
፳፫ ፡ ወኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ።
ጥሩ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ አትጠጣ ።
ኅዳጠ ፡ ወይነ ፡ ቶስሕ ፡ (መዝ ፡፻፬ ፡፲፭) ።
ጥቂት ፡ ወይን ፡ ጨምርበት ፡ እንጂ ።
በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ከብድከ ።
ስለልብህ ፡ ደዌ ።
ወበእንተ ፡ ደዌከ ፡ ዘዘልፍ ።
ስለጀርባህ ፡ ደዌ ፡ አንድም ፡ (በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ከብደከ ፡) ስለጀርባህ ፡ ደዌ ፡ (ወበእንተ ፡ ደዌከ ፡ዘዘ ልፍ ፡) በማስተማር ፡ ጣፊያው ፡ ደርቆ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ።

፳፬ ፡ ቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትዐወቆ ፡ ኃጢአቱ ።
ኢትስተይ ፡ ማየ ፡ ዕራቆ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በትሕርምት፡ ኑሮ ፡ ትሕርምቱን ፡ አፈረስ ፡ ቢሉ ኝስ ፡ ትለኝ ፡ እንደኾነ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ኃጢአቱ ፡ የሚታወቅበት ፡ ሰው ፡ አለ ፡ (አለ ፡) እንዲህ ያደርጋል ፡ ተብሎ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይትባደሮ ፡ ውስተ ፡ ደይን ፡፡

በሞተም ፡ ጊዜ ፡ የሚታወቅበት ፡ ሰው ፡ አለ ፡ (አለ ፡) ዕለቱን ፡ እንዲህ ፡ እንጂ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ ተብሎ

ወቦ ፡ ዘይተልዎ ፡ ኃጢአቱ ፡፡

ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሚታወቅበት ፡ አለ ፡ (አለ ፡) ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ እንጂ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ ተብሎ፡፡

ቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትዐወቆ ፡ ኃጢአቱ ፡፡

እንድም ፡ ኢትሚም ፡ ፍጡን ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የበቃውንና ፡ ያልበቃውን ፡ በምን ፡ እውቀዋለሁ ፡ ትለኝ
እንደኾነ ፡ ከመሾሙ ፡ አስቀድሞ ፡ ኃጢአቱ ፡ የሚታወቅበት ፡ ሰው ፡ አለ ፡፡

ወይትባደሮ ፡ ውስተ ፡ ደይን ፡፡

በተሾመም ፡ ጊዜ ፡ የሚታወቅበት ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ ያደርጋል ፡ ተብሎ ፡፡

ወቦ ፡ ዘይተልዎ ፡ ኃጢአቱ ፡፡

ከተሾመ ፡ በኋላ ፡ ኃጢአቱ ፡ የሚታወቅበት ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ እንጂ ፡ያደርጋል ፡ ተብሎ ፡፡

፳፭ ፡ ወከማሁ ፡ ዘሂ ፡ ይገብር ፡ ሠናየ ፡ ይትዐወቅ ፡ ወዘሂ ፡ ካልእ ፡ ምግባሩ ፡ ኢይትከበት ፡(ገላ ፡፮ ፡፲፱) ፡፡

በጎም ፡ የሚሠራ ፡ ክፉም ፡ የሚሠራ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ አይሰወርም ፡፡

ምዕራፍ ፡ ፮ ፡፡

፩ ፡ ወኵሎ ፡ ነባሬ ፡ ወቅኑይ ፡ አክብሩ ፡ አጋእዝቲክሙ ፡ በኵሉ ፡ (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፩ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፱) ፡፡

ውሉድ ፡ እናት ፡ አባታቸውን ፡ ይርዱ ፡ ብሎ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤት ፡ ጀምሮ ፡ በመካከል ፡ ሌላ ፡ አግብቶበት
ነበርና ፡ ከቀደመ ፡ ነገሩ ፡ ተመለሰ ፡ ቤተ ፡ ሰብእችም ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ጌቶቻችሁን ፡ እርዱ ፡፡

ከመ ፡ ኢይፅርፉ ፡ ላዕለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳይነቅፉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ቤተሰብእ ፡ ለጌታው ፡ ላይገዛ ፡ነው
ብለው ፡፡

ወላዕለ ፡ ትምህርቱ ፡፡

ወንጌልን ፡ እንዳይነቅፉ ፡ በወንጌል ፡ ማመን ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ለጌታው ፡ ላይገዛ ፡ ነው ፡ ብለው ፡፡

፪ ፡ ወእለሰ ፡ ቦሙ ፡ አጋእዝት ፡ መሃይምናን ፡ ኢያስተሐቅሩ ፡፡

ምእመናን ፡ ጌቶች ፡ ያሏቸው ፡ ቤተ ፡ ሰብእችም ፡ ጌቶቻቸውን ፡ አይናቁ ፡ አያቃሉ ፡፡

እስመ ፡ አኃዊሆሙ ፡ እሙንቱ ፡ በሃይማኖት ፡፡

በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ስለኾኑ ፡፡

ዓዲ ፡ ፈድፋደ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎሙ ፡፡

ይልቁንም ፡ አብልጠው ፡ ይገዙላቸው ፡ እንጂ ፡፡

እስመ ፡ ምእመናን ፡ ወፍቁራን ፡ እሙንቱ ፡፡

በሃይማኖት ፡ ስለመሰሏቸው ፡፡

ወለእሉ ፡ ይትዌከፉ ፡ ወይትለአኩ ፡ በፍሥሐ ፡ ሎሙ ፡፡

ትእዛዛቸውን ፡ እየተቀበሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ይርዱቸው ፡፡

ከመዝ ፡ መሀር ፡ ወገሥጽ ፡(ም ፡፬ ፡፲፩ ፡ ቲቶ ፡ ፫ ፡፰) ፡፡

እንዲህ ፡ ምከር ፡ አስተምር ፡፡

ወአስተብቍዖሙ ፡፡

አለዝበህ ፡ ማልዳቸው ፡፡

፫ ፡ ወእመሰቦ ፡ ዘይሜህር ፡ ካልእ ፡ (ገላ ፡፩ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡፡)

እኛ ፡ ከአስተማርነው ፡ ትምህርት ፡ ሌላ ፡ የሚያስተምር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡፡

ወኢይገብእ ፡ ኀበ ፡ ትምህርተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፫) ፡፡

ድኅነት ፡ የሚገኝበትን ፡ ትምህርት ፡ ወደመማር ፡ የማይመለስ ፡፡

ዘውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡

ይኸውም ፡ ወንጌል ፡ ነው ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኀበ ፡ ትምህርተ ፡ ጽድቅ ።
አንድነቱን ፡ ሦስትነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ ወደመማር ፡ የማይመለስ ።

፬ ፡ ውእቱኬ ፡ ዘይትዔበይ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያአምር ።
የሚያውቀው ፡ ሳይኖር ፡ የሚታበይ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ነዋ ።
ዘእንበለ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዘየኃሥሥ ።
መቅሠፍትን ፡ ይሻል ፡ እንጂ ።
ወነገረ ፡ ጋእዝ ።

የጸብእ ፡ የከርከርን ፡ ነገር ፡ ይሻል ፡ እንጂ ።
ዘእምኔሁ ፡ ይመጽእ ፡ ተሐምሞ ።
ምቀኝነት ፡ የሚመጣበት ።
ወተቃንዮ ።
መቃናት ።
ፀሪፍ ። ስው ፡ መሳደብ ።
ምክር ፡ እኩይ ።
ክፉ ፡ ትምህርት ፡ ጠማማ ፡ ምክር ።

፭ ፡ አስተዳምኖ ፡ ሰብእ ፡ ሙሱናን ።
ሰውን ፡ ከሰው ፡ ማጣላት ፡ የሚመጣበት ፡ አንድም ፡ (አስተዳምኖ ፡) ሰውን ፡ ከሰው ፡ ማጣላት ፡(ሰብእ ሙሱናን ፡) ድል ፡ የተነሡ ።
ወውፁኣን ፡ እምጽድቅ ።
ከጽድቅ ፡ የወጡ ።
ወይሬስይዎ ፡ ለጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተግባረ ።
ወንጌልን ፡ መበያ ፡ የሚያደርጉትን ።
ተገኀሦሙ ፡ ለእሉ ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ተለያቸው ።

፮ ፡ እስመ ፡ ለነስ ፡ ተግባረነ ፡ ዓቢይ ፡ ውእቱ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡(ም ፡ ፩ ፡ ፫)፡ፈል ፡ ፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱።
የኛስ ፡ እኮ ፡ ደገኛ ፡ ሥራችን ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ አንድም ፡ የኛ ፡ ደገኛ ፡ ሥራችን ፡ ፈሪሀ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ተገኀሦሙ ፡ ለእሉ ።

፯ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘአምጻእነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ።
ስንወለድ ፡ ይዘነው ፡ የተወለድነው ፡ የለምና ።
ወአልቦ ፡ ዘንክል ፡ ነሢአ ፡ እምኔሁ ፡ (መክ ፡ ፭ ፡ ፲፬) ።
በሞት ፡ ጊዜም ፡ ይዘነው ፡ የምንሔድ ፡ የለምና ።

፰ ፡ እምከመ ፡ ረከብነ ፡ ሲሳየነ ፡ ወአራዘነ ፡ የአከለነ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ፡ ምሳ ፡ ፴ ፡ ፰ ።)
የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ የዓመት ፡ ልብሳችንን ፡ ከአገኘን ፡ ይበቃናል ፡ ኢዮብ ፡ ዕራቅየ ፡ ወፃእኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፡ ወዕራቅየ ፡ እገብእ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ እንዲህ ፡ ለውጦ ፡ እነበበው ፡ በዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ተባብረውብታል ፡ ያዕቆብ ፡ በአሪቱ ፡ እምከመ ፡ ረከብኩ ፡ እክለ ፡ ዘእበልዕ ፡ ወልብሰ ፡ ዘእትኤረዝ ፡ ይከውነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ብሏል ፡ ባለቤቱም ፡ በወንጌል ፡ ሲሳየነ ፡ ዘለለዕለትነ ፡ ብሏል (ማቴ፡ ፮፡ ፲፩፡ ፫ቱ፶ም) በሕንጻ ፡ መነኮሳት ፡ ኢትኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ብሩር ፡ ወወርቅ ፡ አላ ፡ ሥራዕ ፡በዐቅም ፡ ዘየአክል ፡ ለሲሳይከ ፡ ወለአራዝከ ፡ ለሕይወትከ ፡ ብሰዋል ፡ ማሪ ፡ ይስሐቅም ፡ ወለእመ ፡ ተርፈከ እመፍቅደከ ፡ ዕለትከ ፡ ሀበ ፡ ለነዳይ ፡ ወለግዩር ፡ ብሏል ፡ ከዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡አለ ፡ለመነኮሳት ፡ በቁሙ ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ የሰብእ ፡ ዓለም ፡ የዕለት ፡ ያለው ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ የዓመት ፡ ምግብ ፡ የዓመት ፡ ልብስ ።

፱ ፡ ወእለሰ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይብዐሉ ፡ ይወድቁ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ፡(ምሳ ፡ ፳፫ ፡ ፬ና ፡ ፳፰ ፡ ፳፪) ።
ከዚህ ፡ ወጥተው ፡ ሥጋዊ ፡ ክብር ፡ ሊከብሩ ፡ የሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በፍዳ ፡ ይያዛሉ ።
ወብዙኅ ፡ መሣግረ ፡ ፍትወት ፡ ዘዕበድ ፡ ዘይብእሶሙ ፡ ወዘያስጥሞሙ ፡ ለሰብእ ፡ ውስተ ፡ ተሠርዎ ፡ ወሞት ።
ሰዎችን ፡ በመነቀል ፡ ባሕር ፡ የሚያስጥማቸው ፡ ስንፍና ፡ ባመጣው ፡ በፈቲው ፡ ጦር ፡ ይያዛሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፡ እስመ ፡ ሥርዉ ፡ ለኵሉ ፡ እኩይ ፡ አፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡፡
የኃጢአት ፡ ነቁዕ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ነውና ፡ ይወድቁ ፡፡
እስመ ፡ ብዙኃን ፡ በዛቲ ፡ ስሕቱ ፡፡
በዚች ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ከሕግ ፡ የወጡ ፡፡
ወዐለዉ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡፡

ሃይማኖታቸውን ፡ የለወጡ ፡ አሉና ፡ (አለ ፡) አለ ፡ ግያዝ ፡ አለ ፡ ይሁዳ ፡ (ነገ ፡ ካልዕ ፡ ፭ ፡ ፳-፳፯ ፡ ማቴ፡ ፳፮ ፡ ፲፬ ፡ -፲፯ ፡ ማር ፡ ፲፬ ፡ ፲ ፡ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፫-፯) ፡፡
ወኃሠሡ ፡ ለርእሶሙ ፡ ብዙኀ ፡ መቅሠፍተ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭-፳፩ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፭) ፡
በራሳቸው ፡ መቅሠፍትን ፡ የሚያመጡ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ (ለርእሶሙ) ራሳቸውን ፡ ለመጉዳት ፡፡

፲፩ ፡ ወአንተሰ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጐየይ ፡ እምዝ ፡፡
ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጢሞቴዎስ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ራቅ ፡፡
ወዴግን ፡ ጽድቀ ፡ (፪ኛ ጢሞ ፡ ፪ ፳፪ ፡ ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬) ፡
ጽድቅን ፡ ተከተል ፡(አለ) አጽንተህ ፡ያዝ ፡፡

ወምሂረ ፡	ማስተማርን ፡፡
ወሃይማኖተ ፡	ሃይማኖትን ፡፡
ወተፋቅሮ ፡	ፍቅርን ፡
ወትዕግሥተ ፡	ትዕግሥትን ፡፡
ወትሕትና ፡፡	ትሕትናን ፡ አጽንተህ ፡ ያዝ ፡፡

፲፪ ፡ ተጋደል ፡ ሠናየ ፡ ገድለ ፡ በሃይማኖት ፡(፩ ቆሮ ፡፱ ፡፳፭ ፡፳፯) ፡፡
በሃይማኖት ፡ ጸንተህ ፡ በጎ ፡ ገድልን ፡ ተጋደል ፡፡
ለተመጥዎ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘሎቱ ፡ ተጸዋዕከ ፡፡(ፊል ፡፫ ፲፪ ፡፲፬) ፡
በሃይማኖት ፡ የተጠራህባት ፡ የማታልፍ ፡ መንግሥት ፡ ስማይን ፡ ለመውረስ ፡
ወአመንከ ፡ ሠናየ ፡ እሚነ ፡ በቅድመ ፡ ብዙኃን ፡ ሰማዕት ፡፡

በብዙ ፡ ምስክር ፡ ፊት ፡ በጎ ፡ እምነት ፡ ያመንህለት ፡ ወገዘሮ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ በአንተ ፡ አይሁድ ፡አለ፡
ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ እንዲል ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡(፲፮ ፡፫) ፡፡

፲፫ ፡ ከመዝ ፡ እኤዝዘከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ሙታነ ፡ ያሐዩ ፡ (ዘዳግ ፡፴፪ ፡፴፱) ፡
ሙታን ፡ ሕሊናን ፡ ትንሣኤ ፡ ሕሊና ፡ ሙታን ፡ ሥጋን ፡ ትንሣኤ ፡ ሥጋ፡በሚያሥነሣቸው፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ አዳኝብሃለሁ ፡፡
ወኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ፊት ፡ አዳኝብሃለሁ ፡፡
ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በቅድመ ፡ ጲላጦስ ፡ ጳንጤናዊ ፡ (ዮሐ ፡፲፰ ፡፴፮ ፡፲፱ ፡፲፩ ፡፡)
በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡፡እንድም ፡ አንሰ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መጻእኩ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ
ተወለድኩ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ሰማዕተ ፡ በጽድቅ ፡ ብሎ ፡ የመሰከረ ፡ (ዮሐ ፡፲፰ ፡፴፯ ፡፡)

፲፬ ፡ በሠናይ ፡ አሚን ፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ በንጽሕ ፡፡
እኤዝዘከ ፡ በሠናይ ፡ አሚን ፡ ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በሠናይ ፡ አሚን፡ ከመ ፡ ትዕቀብ ፡ በሠናይ ፡ አሚን፤)
በበ ጐው ፡ ጸንተህ ፡ ብንጽሕና ፡ ኾነህ ፡ ይህን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ አዳኝብሃለሁ ፡፡
እንዘ ፡ ኢታደሉ ፡፡
በፍርድ ፡ በብያኔ ፡ በጸሎት ፤ በትምህርት ፤ በምጽዋት ፡ ፊት ፡ አይተህ ፡ ሳታዳላ ፡፡
እስከ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከሚመጣበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡፡

፲፭ ፡ ዘያስተርኢ ፡ በዕድሜሁ ፡
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የሚገለጽ ፡፡
ዘባሕቲቱ ፡ ብፁዕ ፡(ም ፩ ፡፲፩ ፡፡)
እሱ ፡ ብቻ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፣ የሚኾን ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኃያል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት እግዚአ ፡ አጋዕዝት ፡ (ራእ ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ፡ ዘዳግ ፡ ፲ ፤ ፲፯ ።)
ኃያል ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ እግዚአ ፡ አጋእዝት ፡ የሚኾን ።

፲፮ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ።
እሱ ፡ ብቻ የማይሻር ።
ዘኢይመውት ።
ኅልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለበት ፡
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍእ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።
ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የማይጠፉ ፡ ብርሃን ፡ ያለው ፤ ኅልፈት ፡ ጥፋት ፡ የሌለው ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ፡(ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።)
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ያየው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ሊያየው ፡ የሚችል ፡ የሌለ ።
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍዕ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።
አንድም ፡ የማይለይ ፡ ዕውቀት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚቻለው ፡ የሌለ ።
ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍዕ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።
አንድም ፡ የማይመረመር ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ።
ዘአልቦ ፡ ዘርእዮ ፡ ሰብእ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የመረመረው ፡ የሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ርእዮቶ ።
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ሊመረምረው ፡ የሚቻለው ፡ የሌለ ።
ዘሎቱ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ወኃይል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ክብር ፡ ጌትነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚኾን ።
አሜን ። በእውነት ።

፲፯ ፡ ለአብዕልተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ አዝዞሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትአበዩ ።
የዚህን ፡ ዓለም ፡ ባለጸጎች ፡ እንዳይታበዩ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወኢይትአመንዎ ፡ ለብዕሎሙ ፡ ኃላፌ ፡ ዘእንበለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡(መዝ ፡ ፷፪ ፡ ፲፩ ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፳፬)
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፡ ኃላፊውን ፡ ከብት ፡ እንዳይተማመኑ ፡ አንድም ፡ በሕያው ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ እንጂ ፡ በኃላፊው ፡ ከብት ፡ እንዳይመኩ ።
ዘውእቱ ፡ ይሁበነ ፡ በብዝኀ ፡ ብዕሉ ፡ ኵሎ ።
በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ኹሉን ፡ የሚሰጠን ።
ከመ ፡ ንትፈሣሕ ።
ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ።

፲፰ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ግብረ ፡ ሠናየ ።
(አዝዞሙ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ሠናየ ፡) በጎውን ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ምክራቸው ፡ አስተምራቸው ።
ወይብዐሉ ፡ በገቢረ ፡ ጽድቅ ።
በትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ይከብሩ ፡ ዘንድ ።
ወይኩኑ ፡ ራትዓነ ።
ቅኖች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።
ወጺጋውያነ ።
ለጋሶች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።
ወሱቱፋነ ።
እነዚያ ፡ በመስጠት ፡ ነዳያን ፡ በመቀበል ፡ ለጸሎት ፡ አንድ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱ ፡ ወይማርሩ ፡ ለርእሶሙ ፡ መሠረተ ፡ ሠናየ ፡ ለዘይመጽእ ፡ ዓለም ።

ለሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ለራሳቸው ፡ በጎ ፡ ቢጋርን ፡ ይበጉሩ ፡ ዘንድ ፡ (እስ ፣)በጎ ፡ ተስፋን፡ ይይዙ፡ዘንድ

ከሙ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘበአማን ፡(ማቴ ፡፲ ፡፳ ።)

የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ መንግሥት ፡ ለማይን ፡ ለመውረስ ።

፳ ፡ ኦ ጢሞቴዎስ ፡ ዕቀብ ፡ ማኅፀንተከ ፡ (፩፡ ጢሞ ፡፩ ፡፲፬ ።)

ጢሞቴዎስ ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ። አንድም ፡ አደራህን ፡ ጠብቅ ።

ተገኀሦሙ ፡ ለርኩሳን ፡ እለ ፡ ያመጽኡ ፡ ነገረ ፡ ከንቶ ፡ (፩፡ ጢሞ ፡፬ ፡፯ ።)

ከንቱ ፡ ነገርን ፡ የሚያመጡ ፡ ድል ፡ የተነሡ ፡ ሰዎችን ፡ ተለያቸው ።

ወያሌልዎ ፡ ለጽድቅ ፡ በሐሰት ።

ጽድቅን ፡ በኃጢአት ፡ እውነትን ፡ በሐሰት፣ አምልኮትን ፡ በክህደት ፡ ወንጌልን ፡ በኦሪት ፡ የሚለውጡ

ትን ፡ ተለያቸው ።

፳፩ ፡ እለሙ ፡ እሉ ፡ በሕቱ ፡ እምተሰፉ ፡ ሃይማኖት ።

ሕለሁ ፡ እምና ፡ ከሚገኘው ፡ ተስፋ ፡ ወጥተዋልና ።

ጸጋ ፡ ምስሌከ ፡(ም ፡፩ ፡፳ ፡፪ ጢሞ ፡፬ ፡፲፰ ።)

ጸጋ ፡ አድሮብህ ፡ ይኑር ።

አሜን ።　　　　　　　　በእውነት ።

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በአቴና ፡ ወተፈነወ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ።

በአቴና ፡ የተጻፈ ፡ በቲቶ ፡ እጅ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ የተላከ ፡ መጀመሪያ ፡ ክታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሕንሚሎቶ ፡ [illegible] ገባው ።

www.ethiopianorthodox.org